# የ1ኛ ተሰሎንቄ ጥናት(31)

## ጥናት አንድ ሐዋ ሥራ 17፡1-10

የጥናት ዓላማ፡- ሳይቀየጥና ሳይበረዝ የተሰበከ የክርስቶስ ወንጌል፤ የአይሁድ ሆነ የግሪክ፣ የወንድ ሆነ የሴት፣ ወይም የሃብታም ሆነ የደሃን ልብ ለመለወጥ የሚችል የእግዚአብሄር ብርቱ ሃይል እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹አይሁድም አንዳንዶቹ የሰሙትን በመቀበል ከጳውሎስና ከሲላስ ጋራ ተባበሩ፤ ደግሞም ቁጥራቸው ብዙ የሆነ እግዚአብሄርን የሚፈሩ ግሪኮችና አያሌ እውቅ ሴቶች የሰሙትን ተቀብለው ከእነርሱ ጋራ ተባበሩ፡፡›› ሐዋ ሥራ 17፡4

1. ሐዋ ሥራ 17፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ ጳውሎስና ሲላስ በተሰሎንቄ እንደደረሱ ያደረጉት የመጀመሪያ ነገር ምንድነው? በቁ2 ላይ ሉቃስ ስለ ጳውሎስ የሚናገረው የምታየው አንድ ነገር ምንድነው? ሉቃስ ስለ አንተ ወይም አንቺ ቢጽፍ እንደልማዱ ቅዱሳን መጻህፍትን ለሰዎች ከፈተ ይል ይሆን?
2. በቁ3 መሰረት በምኩራብ ለተገኙት ሰዎች ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ የነገራቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምን ነበሩ? በዚሁ ቁጥር ላይ አስረግጠው እንዲያውቁት የፈለገው አንድ ነገርስ ምን ነበረ?
3. የእግዚአብሄር ቃል በሰዎች ህይወት መስራት ሲጀምር የሆነው ነገር ምን ነበረ? እነዚህ አይሁዶች የቀኑበት ምክንያትስ ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ?
4. ‹‹ኢያሶንም በቤቱ ተቀብሏቸዋል›› የሚለውን ስንበለከት ይህ ሰው እንደተባለው ያደረገ ከሆነ፣ እየታዘዘ ያለው በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ ትዝ የሚልህን ጥቅስ ተናገር፡፡ ለዚህ ሰው እነጳውሎስን መቀበሉ አደገኛ ሆኖ የሚገኘው ለምንድነው ትላለህ? ዋጋ የሚያስከፍሉትን የጌታ ትዕዛዞች ለመታዘዝ ምን ያህል ዝግጁ ነህ?
5. በቁ7 ላይ ክርስትያኖች የቀረቡባቸው ክሶች ምን የሚሉ ነበሩ? እነዚህ ክሶች በእውነት ላይ የተመሰረቱ ናቸው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን?
6. የከተማውን ህዝብና ሹማምንቱን ያሸበረው ነገር ምን ነበረ? ጳውሎንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ ያስፈለገበት ምክንያትስ ምንድነው ትላለህ?
7. ወደ ቁ4 ተመልሰን በጳውሎስ ያመኑትን ስንመለከት እነማንን ያካትታል? ይህንን ስንመለከት፤ የክርስቶስ እውነተኛ ወንጌል ሳይሸቀጥና ሳይቀየጥ መሰበክ ሊያስገኝ ስለሚችለው ውጤት ምን ማየት እንችላለን? ሰዎችን ሊያድን ሃይል ያለው ንጹህ የክርስቶስ ወንጌል ስለሆነ ለማበጃጀት ሳትሞክር የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ ማስማት ለሰዎች ህይወት መዳን መልስ እንደሚሆን አትጠራጠር፡፡

# ጥናት ሁለት 1ኛ ተሰ 1፡1-10

የጥናት ዓላማ፦ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቤተ ክርስትያን፣ አንዳችን ከሌላችን ብርታት ልንማር የምንችለው ነገር ሊኖር እንደሚችል በማመን በትህትና ልባችንን ማዘጋጀት እንደሚኖርብን ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹…ብርቱ መከራ ቢደርስባችሁም ቃሉን በመንፈስ ቅዱስ ደስታ ተቀብላችኋል፡፡ ከዚህም የተነሳ በመቄዶንያና በአካይያ ለሚገኙ መእመናን መልካም ምሳሌ ሆናችኋል፡፡›› 1ኛ ተሰ 1፡7

1. 1ኛ ተሰ 1፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ በመጀመሪያዎቹ ቁጥሮች ስንመለከት ሰላምታው የመነጨው ከማን ነው? ሰላምታ ተቀባዮቹስ እነማን ናቸው? ደብዳበው የተጻፈላቸው ሰዎች ንብረትነታቸው የማን የማን እንደሆነና ይህ ምን ማለት ሊሆን እንደሚችልም አስረዱ፡፡
2. በቁ3-4 መሰረት ጳውሎስና ባልደረቦቹ ስለተሰሎንቁ ሰዎች የሚያደርጉት አንድ ነገር ምንድነው? እነዚህ ሰዎችን ለምስጋና የሚያነሳሷቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆነ ዘርዝር፡፡
3. በቁ3 ከምንመለከተው እውነት በመነሳት፤ ሥራ ሊመነጭ የሚገባው ከምንድነው? በክፍሉ መስረት አማኝ ለእግዚአብሄር ሥራም ሆነ ሌሎችን ለመርዳት ሲደክም ራሱን መጠየቅ የሚኖርበት ጥያቄ ምንድነው? የተሰሎንቁ ሰዎች በመልካም አጀማመር ላይ እንዳሉ የሚጠቁመን ነገር ምንድነው?
4. ቁ5-7ትን ስናይ እነ ጳዎሎስ የተሰሎንቁ ሰዎች በእግዚአብሄር መመረጣቸውን ስላረጋገጡበት የሰጠው አንድ ምክንያት ምንድነው? ወንጌል ወደተሰሎንቁ የመጣባቸውን መነገዶች ዘርዝር፡፡
5. በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ተገልጋዮቹና አገልጋዮቹ ክርስትያናዊ ሃላፊነታቸውን ተወጥተዋል ሊያሰኘን የሚችው የትኛው ሃሳብ ነው ትላለህ? የጌታንን የነጳውሎስን ፈለግ መከተላቸው በእነርሱ ህይወት ደግሞ ያስከተለው ነገር ምን ታያለህ? ቁ7ትን ተመልከት፡፡
6. በቁ8-10 መሰረት የተሰሎንቁ ሰዎችን እምነት አስመልክቶ በየሥፍራው የሚነገርላቸውን ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ እንደ ተሰሎንቁ ሰዎች ከዓለምና ጣዖታትን ከማምለክ የተመለስን ሁላችን ህያውንና እውነተኛውን አምላክ ለማገልገል እንደሆነ ገብቶን እያገለገልነው ነው ወይ?
7. 1ኛ ተሰ 2፡14 ላይ በምሳሌነት የሚነገርለት የትኛው ቤ/ክ ለየትኛው ቤ/ክ ነው? 1ኛ ተሰ 1፡7-8 በምሳሌነት የተጠቀሰው የትኞቹ አማኞች ለየትኞቹ አማኞች ነው? 2ኛ ቆሮ 8፡1-8 በተለይም ቁ8 ላይ በማተኮር ምሳሌ የሆነው የትኛው ቤ/ክ ለየትኛው ቤ/ክ ነው?
8. ከእነኚህ ከተለያዩት አማኞች ወይም አብያተ ክርስትያናት ጎዶሎነት የሌለበት ታያለህ ወይ? ሁሉም አብያተ ክርስትያናት ከሌላኛው ሊማር የሚችለው ነገር መኖሩ ስለራሳችን ሁኔታ ምን ያስረዳናል? በግልህም ሆነ እንደ ቤተክርስትያን ከሌሎች ለመማር ምን ያህል ልብህ ክፍት ነው? ከሌላው ለመማር ክፍት ያልሆነ በህይወቱ ለማደግ እድሉ የመነመነ ነውና በጌታ ጸጋ ልብህን አዘጋጅ፡፡

# ጥናት ሶስት 1ኛ ተሰ 2፡1-9

የጥናት ዓላማ፡- በየግል ኑሯችንም ሆነ በማናቸውም በተሰማራንበት አገልግሎት ያሰማራንን እግዚአብሄርን እንጂ ማንንም ሰው ደስ ለማሰኘት እንዳልተሰለፍን እንድናውቅና ሰዎችም እንዲያውቁት የማድረግ ሃላፊነት እንዳለብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ይህንን የምናደርገው ልባችንን የሚመረምረውን እግዚአብሄርን እንጂ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት ብለን አይደለም፡፡›› 1ኛ ተሰ 2፡4

1. 1ኛ ተሰ 2፡1-9 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2 ጳውሎስና ባልደረቦቹ ወደ ተሰሎንቄ መምጣታቸው ከንቱ እንዳልነበረ የሚያምኑበት ምክንያት ለምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች መሰረት፤ ወንጌል ወደዚህች ከተማ የደረሰበት ሁኔታ እንደነበረ ተናገር፡፡
2. ቁ3-4 ትን ስታነብ እነዚህ ሰዎች ወንጌልን አናቀርብም የሚሉባቸው ሶስቱ ሁኔታዎች ምን ምንድናቸው? ወንጌልን እንናገራለን የሚሉበትስ አንዱ መንገድ ምንድነው?
3. በቁ4-5 አነጋገር ከስህተት፣ ከማታለልና፣ በክፉ ዓላማ ከመስበክ ይልቅ በእግዚአብሄር እንደተላከ ሰው መስበክን የመረጡበት ምክንያት ለምንድነው? በተለይ በቁ5 መሰረት ሲሰብኩ ያልተጠቀሙባቸው ሁለት ዘዴዎች ምንና ምን ነበሩ? በህይወትህና በአገልግሎትህ እነዚህ ሁለት ነገሮች እንዳይገቡ ምን ያህል ትጠነቀቃለህ?
4. ከላይ ባየነው ክፍል እነጳውሎስ አገልግሎታቸው እንደሚናገሩት ለመሆኑ ምስክር አድርገው የሚጠሩት ማንን ነው?
5. በቁ6-7 መሰረት በጳውሎስ አነጋገር ከተሰሎንቄ ሰዎችም ሆነ ከሌሎች ከሚያገለግሏቸው ሰዎች የማይጠብቁት አንድ ነገር ምንድነው? በዚሁ ክፍል ውስጥ ጳውሎስና ባልደረቦቹ መብታቸው የሆነ ነገር ግን ያልተጠቀሙበት ነገር ምንድነው?
6. በቁ7 ላይ ጳውሎስ ራሱን እንደማን አድርጎ ነው የሚያቀርበው? ይህንንስ ስላመጣበት ምክንያት ክፍሉ ምን ይነግረናል? ‹‹እናት ልጅዋን እንምትንከባከብ እኛም በመካከላችሁ በየዋህነት ተመላለስን፡፡›› ተመላለስን የሚለው ቃል በዚህ ሃሳብ ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ለምን ይመስልሃል?
7. ቁ8-9ኝን ስናነብ አገልጋዮቹ ቅዱሳኑን ከመውደዳቸው የተነሳ ለማካፈል ፈቃደኛ የሆኗቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በቁ2 ና በቁ8 መሰረት የወንጌል ባለቤት ማን እንደሆነ ነው የምናየው? ባለቤቱን ማወቃችን በአንተ አስተያየት ለምንሰብከው መልዕክት ምን አስተዋጽዖ አለው ትላለህ?
8. በቁ9 መሰረት ወንጌሉን ሲሰብኩ ስላሳለፉት ሁኔታስ ምን ትመለከታለህ? በቁ4 መነጽር ስንመለከተው ‹‹ይህንን የምናደርገው…›› ለምንድነው ይላል? አንተስ ብዙ ስትጥር፣ ብዙ ስትደክም፣ ሌሊትና ቀን ስትሰራ ማንን ደስ ለማሰኘት ነው? በኑሮና በአበልግሎትሁ ሁሉ ትኩረትህ ሰውን ሳይሆን እርሱን ማስደሰት ብቻ ይሁን፡፡

# ጥናት አራት 1ኛ ተሰ 2፡10-20

የጥናት ዓላማ፡- የኑሯችንንና የአገልግሎታችን ትኩረት ሊሆን የሚገባው፣ ዛሬ ልናገኝ በምንችላቸው የተለያዩ ምድራዊ ነገሮች ላይ እንዳልሆነና ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ልንቀበል ባለው እጅግ የተሻለ በረከት ላይ ሊሆን እንደሚገባው ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ በእርሱ ፊት ተስፋችን ወይም ደስታችንወይም አክሊላችን ማን ነው? እናንተ አይደላችሁምን?›› 1ኛ ተሰ 2፡19

1. 1ኛ ተሰ 2፡10-20 በአንድነት ይነበብ። ጳውሎስና ባልደረቦቹ በቁ10 ላይ በምስክርነት የሚጠሩት እነማንን ነው? እነዚህ ምስክሮች ሊመሰክሩ እንደሚችሉ የተነገረላቸው ስለምንድነው? አንተስ እነዚህን ነገሮች አስመልክቶ ስላኗኗርህ ምስክር ሊሆንህ የሚችል መጥራት ትችላለህ ወይ?
2. በቁጥር 10 ላይ ከተጠቀሰው ሌላ በቁ11-12 አነጋገር የተሰሎንቄ አማኞች እንደሚያውቁት የተናገራቸው አንድ እውነት ምን ነበረ? እነዚህን ሰዎች እንደልጅ በመቁጠር ያደርጉት ከነበሩት ነገሮች መሃል የጠቀሳቸው ነገሮች ምንድናቸው?
3. በቁ13 ላይ የጳውሎስ ያለማቋረጥ የምስጋና ምክንያት የሆነው ነገር ምንድነው? ሰዎች የእግዚአብሄርን ቃል እንደ እግዚአብሄር ቃልነቱ ሲቀበሉት ስናይ ምን ያህል መደሰትና ለምስጋስ ያነሳሳናል?
4. በቁ14 ላይ ስንመለከት የተሰሎንቄ አማኞች ከይሁዳ አማኞች ጋራ የሚመሳሰሉበት መንገድ ምንድነው? ቁ7 ‹‹እናት ልጆዋን›› ቁ11 ‹‹አባት ለገዛ ልጆቹ›› ቁ14 ‹‹ወንድሞች ሆይ›› የሚሉት አነጋገሮች በአመኞች መሃል ስላለው ግንኙነት የሚያሳየው ነገር ምንድነው?
5. በቁ15-16 ላይ ‹‹እነርሱ›› እያለ የሚናገረው ስለማን ነው? እነዚህ ሰዎች ስላደረጓቸው ነገሮች የተነገሩትን ሁሉ ዘርዝር። ይህንን ሁሉ የሚያደርጉት ለምንድነው? ሃይማኖተኛነት አንዳንድ ጊዜ ወደ እግዚአብሄር ከማቅረብ ይልቅ የእግዚአብሄር ጠላት ሊያደርግ ስለሚችል ልንጠነቀቅ ይገባናል።
6. በቁ17-18 አነጋገሩ ጳውሎስ ለእነዚህ ክርስትያኖች ስላለው ስሜት ምን መረዳት እንችላለን? ፍቅራቸው የቃል ብቻ እንዳልሆነና ፍቅራቸውን ለመግለጥ የወሰዷቸው እርምጃዎች ምን ታያለህ? እኛስ ለወገኖች ያለንን ፍቅር በተግባር ለመግለጥ የምናደርገው ሙከራ አለ ወይ?
7. ቁ19-20ን በማንበብ ‹‹ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ›› የሚለው ሃሳብ ጳውሎስ ምጻቱን አስመልክቶ ስላለው አመለካከት የሚያረጋግጥልን ቁልፍ እውነት ምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እነጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች እንዴት ነው የሚመለከቷቸው?
8. የጳውሎስ ኑሮና አገልግሎት በነዚህ የመጨረሻ ቁጥሮች መነጽር ሲታይ፣ ትኩረቱ በአሁን ላይ ነው ወይስ በሚመጣው (በወደፊቱ)? ለምን ይህንን ማለት ቻልክ? ያንተስ ኑሮህን አገልግሎትህ ያተኮረው በየትኛው ላይ ነው? በዛሬው ወይስ ጌታ ሲመጣ በምታገኘው?

# ጥናት አምስት 1ኛ ተሰ 3፡1-13

የጥናት ዓላማ፡- ከእግዚአብሄር ቃል ውስጥ እየመረጥን ሰዎች ሊሰሙ የሚወዱትን ሃሳብ ብቻ የምንሰብክ ሳይሆን በቃሉ ውስጥ የሰፈረውን እውነት ሁሉ ሳናስቀር የመናገር ሃላፊነት እንዳለብን ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹በእርግጥ ከእናንተ ጋራ በነበርንበት ጊዜ መከራ እንደሚደርስብን በየጊዜው እንነግራችሁ ነበር፤ እንደምታውቁትም እንዲሁ ደግሞ ሆኖአል፡፡›› 1ኛ ተሰ 3፡4

1. 1ኛ ተሰ 3፡1-13 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ላይ መታገስ አልቻልንም እያለ የሚናገረው ምኑን ነው? በዚህ ክፍል ስናነብ ጢሞቲዎስ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተላከበት ምክንያት ለምንድነው? እነጳውሎስ ጢሞቲዎስን ወደዚያ በመላክ መስዋዕት ከፍለዋል ማለት የሚያስችለን ነገር ምንድነው?
2. ቁ3ትን ስናይ የጢሞቲዎስ ተልዕኮ በይበልጥ ወቅታዊና አስፈላጊ መሆኑን የሚያረጋግጥልን ነገር የትኛው ነው? ‹‹እኛም ለዚህ ነገር እንደተመደብን…›› ከሚለው አነጋገር ምን ትረዳለህ?
3. የጳውሎስ ፍርሃት በቁ5 ላይ ስለነዚህ አማኞች ምን ነበረ? ከላይ ባሉት ቁጥሮች ላይ ካየነው ሌላ ስለጢሞቲዎስ ተልዕኮ ይህ ክፍል ምን ተጨማሪ ሃሳብ ይሰጠናል? አንተስ ወገኖች በጠላት ፈተና እንዳይወድቁ ምን ያህል ድጋፍና ጥረት ታደርጋለህ?
4. ጢሞቲዎስ የተላከው ቁ1 ፍቅራቸውን መታገስ ስላልቻሉ፣ ቁ5 ደግሞ የእምነታቸውን ሁኔታ መታገስ ስላልቻሉ ሲሆን የጢሞቲዎስ ሪፖርት በቁ6 ላይ ከነዚህ ሁለት ነገሮች አንጻር ምን ያረጋግጣል? የነጳውሎስ ፍርሃት መሰረት ነበረው ትላለህ ወይ? ለምን? አንዳንድ ጊዜ ለእግዚአብሄር ለራሱ አሳልፎ አደራ መስጠት ከማያስፈልግ ጭንቀት ያድነናል፡፡
5. በቁ7-9 ላይ ለእነጳውሎስ መጽናናት የሆናቸው ነገር ምንድነው? የእነዚህ አማኞች በእምነት መበርታት ለጳውሎስና ለጓደኞቹ በተጨማሪ ያስገኘው ነገር ምን ነበረ? ይህንን ያህል ደስ የተሰኙበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? የወገኖች በእምነታቸው መጽናት በአንተ ውስጥ በነጳውሎስ ውስጥ የፈጠረውን ስሜት ይፈጥራል ወይ?
6. ቁ10-11 ስንመለከት እነጳውሎስ የተሰሎንቄን ክርስትያኖች በድጋሚ ለማግኘት የቆረጡ መሆናቸውን በምን እንረዳለን? ‹‹ሌሊትና ቀን…እንጸልያለን›› ሲሉ ወንጌል መስበክም ሳይኖር ቀንም ማታም በጸሎት ጊዜውን እናሳልፋለን ማለታቸው ነው ወይ? አስረዳ፡፡
7. በቁ12-13 ላይ ጳውሎስ የሚጸልይላቸውን ሁለት ጸሎቶች ተናገር፡፡ አንተስ በየትኛው አቅጣጫ ነው የበለጠ ጸሎት የሚያስፈልግህ?
8. ወደ ቁ4 ተመልሰን ስናነብ ለተሰሎንቄ ክርስትያኖች በተደጋጋሚ የተነገራቸው አንድ ነገር ምን ነበረ? ከዘመኑ ትምህርት ማለትም አማኝ ደልቶትና ተመችቶት እንጂ መከራ ሊደርስበት አያስፈልግም ከሚለው ጋራ ይህንን አመለካከት እንዴት ታስታርቀዋለህ? ጳውሎስ በሐዋ 20፡27 የተናገረው ከዚህ ድርጊቱ ጋራ የሚሄደው እንዴት ነው? የእግዚአብሄር አገልጋይ ሰዎች ሊሰሙ የሚሹትን እየመረጠ የሚናገር ሳይሆን የእግዚአብሄርን ቃል ሳይጨምርና ሳይቀንስ ማስተላለፍ ሃላፊነቱ ነው፡፡

# ጥናት ስድስት 1ኛ ተሰ 4፡1-10

የጥናት ዓላማ፡- በህይወታችን ማናቸውም ዓይነት የመንፈስ ፍሬ ሆነ መልካም ባህርይ፤ እለት እለት እያደገና እየጨመረ የሚሄድ እንጂ ደረስኩ ወይም በቃ ብለን የምንረካበት ሁኔታ ሊኖር እንደማይገባን ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹በመላይቱ መቄዶንያ የሚገኙትን ወንድሞች ሁሉ እንደምትወዷቸው የታወቀ ነው፤ ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ከዚህ በበለጠ እንድትገፉበት እንመክራችኋለን።›› 1ኛ ተሰ 4፡10

1. 1ኛ ተሰ 4፡1-10 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 አነጋገር መሰረት የተሰሎንቄ ሰዎች የተማሩት ነገር ምን ነበረ? እነዚህ አማኞች በተማሩትና በኑሯቸው መሃል ልዩነት ይታያል ወይ?
2. በነዚሁ ቁጥሮች ላይ ስናይ እነጳውሎስ የሚለምኗቸው ምን እንዲያደርጉ ነው? በአንድ በኩል ‹‹የምንለምናችሁ›› እያለ ሲናገር በሌላ በኩል ደግሞ ‹‹በጌታ በየሱስ ስልጣን›› እያለ ይናገራል። ለምን ይመስልሃል ሁለት ተቃራኒ የሚመስሉ አነጋገሮችን የሚጠቀመው?
3. ቁ3-4 ስናነብ የእግዚአብሄር ፈቃድ ሆነው የተጠቀሱ ሶስት ሃሳቦችን ተናገር። ሰው እነዚህን ነገሮች አስመልክቶ ምን ማድረግ እንደሚኖርበት ወደ እግዚአብሄር መጸለይ የማይኖርበት ለምንድነው?
4. ቁ5-6 እነጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች ከላይ የተነገሩትን ሃጥያቶች አስመልክቶ ቀደም ብለው እንዳደረጉ የሚጠቅሱላቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እንደዚህ አይነት ነገሮች የማን ተግባር እንደሆኑ ነው የምናነበው? እግዚአብሄር በዚህ ነገር እንደማይቀልድ የምናየው እንዴት ነው?
5. ለምን እንደተጠራንና ለምን እንዳልተጠራን በቁ7 ጳውሎስ ያሰፈረውን ተናገር። ለምንድነው እግዚአብሄር ለቅድስና የጠራን ብለህ ታምናለህ? ከዚህ ጋራ የሚሄድ ትዝ የሚልህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የትኛው ነው?
6. ቁ8 ላይ የእግዚአብሄርን ቃል ሰዎች በስብከትም ሆነ በትምህርት ወይም በምክር ሲነግሩን ለመስማትና ለመታዘዝ እንቢ ለምንል ሰዎች መልዕክቱ ምንድነው? ሰዎች ቃሉን ነግረሃቸው ለመታዘዝ እንቢ ቢሉ ሃላፊነትህ ምንድነው ብለህ ታስባለህ? ልብህ ለቃሉ ዛሬም ይንቀጠቀጣል ወይስ ድፍረት ልብህን ሞልቶታል?
7. የተሰሎንቄ ክርስትያኖች በመሃላቸው ከፈሰሰው በረከት አንደኛው በቁ9 ላይ የምናየው ነገር ምንድነው? ለምንድነው ይህ ነገር በዘመናት ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኘው? የወንድማማች ፍቅር ከቤተክርስትያን ከመጥፋቱ የተነሳ የወንጌልን ሥራ ለመስራት ሲያስቸግር አይተህ ታውቃለህ ወይ?
8. በቁ10 ላይ የነጳውሎስ ምክር ምን የሚል ነው? በቁ9፣10 እና በተለያዩ ቦታዎች እነዚህ ሰዎች ፍቅር እንዳላቸው ተመልክተናል፤ ለምን ይመስልሃል የበለጠ እንዲገፉበት የሚመከሩት?

# ጥናት ሰባት 1ኛ ተሰ 4፡11-18

የጥናት ዓላማ፡- እኛ አማኞች ራሳችንን በማናቸውም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ስናገኘው፤ የክርስቶስን ዳግመኛ መምጣትና የእኛንም ከክርሱ ጋራ የመሆን ተስፋ እያሰብን አንዳችን ሌላችንን የምናጽናናበት የከበረ ተስፋ ሊሆነን እንደሚገባ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹…በዚህም መሰረት ለዘለዓለም ከጌታ ጋር እንሆናለን፡፡ ስለዚህ በዚህ ቃል እርስ በእርሳችሁ ተጽናኑ፡፡›› 1ኛ ተሰ 4፡18

1. 1ኛ ተሰ 4፡11-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ11-12 ላይ እነጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች ሲሰጡ የምናያቸው ሶስት ትዕዛዞች ምን ምንድናቸው? ትዕዛዞቹን ሲሰጧቸው ስንተኛ ጊዜያቸው ነው? 3፡4 ‹‹በየጊዜው እንነግራችሁ ነበር›› 6፡6 ‹‹ከዚህ በፊት እንደነገርናችሁ›› 4፡11 ‹‹ከዚህ በፊት እንዳዘዝናችሁ›› ከሚሉት አነጋገሮች አሰራር ምን ትማራለህ?
2. እነዚህ ክርስትያኖች ሶስቱን ነገሮች እንዲያደርጉ የታዘዙባቸው ሁለቱ ዋነኛ ምክንያቶች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ በምን ዓይነት ነው እነዚህ ነገሮች በውጭ ያሉትን ሰዎች ሊነኩ የሚችሉት?
3. ከነዚህ ከሶስት ትዕዛዛት መካከል በራስህ ህይወትም ሆነ ባለህባት ቤተ ክርስትያን አስቸጋሪ ሆኖ የምታየው የትኛቸውን ነው? በራስ ጉዳይ ላይ ብቻ አለማተኮር የሚያስከትላቸው ነገሮች ምንድናቸው ብለህ ታምናለህ? አንተስ በሰዎች ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ላለመግባትና በራስህ ጉዳይ ላይ ብቻ ለማተኮረ ምን ያህል ትጥራለህ?
4. በቁ13 መሰረት ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች እንዲያውቁ የሚፈልገው ነገር ምንድነው? በዚህ ክፍል አማኞችን ከማን ጋራ በማነጻጸር ነው የሚናገረው? ክርስትያኖች ሃዘን ማዘን የለባቸውም ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ ነው?
5. በጌታ ያንቀላፉ ሰዎች ከሙታን ይነሳሉ ብለን ለማመን በቅድሚያ ማመን የሚኖርብን እውነት በቁ14 መሰረት ምንድነው? 1ኛ ቆሮ 15፡12-14 ጳውሎስ ለዚህ ምክንያት አድርጎ የሚናገረው ነገር ምንድነው?
6. በቁ16 ላይ ‹‹አስቀድመው ይነሳሉ›› ሲል ከምን አስቀድሞ ማለቱ ነው? መልስህን ከዛሬው ምንባብ ውስጥ ቢያንስ ሁለት ክፍሎችን በመጠቀም ደጋፊ ሃሳብ ተናገር፡፡
7. ቁ16 ኢየሱስ ከሰማይ በምን ሁኔታ እንደሚገለጥ ሲናገር የሚጠቅሳቸው ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ከቁ 15-18 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የሰፈሩትን ቢያንስ አራት የሚሆኑ ነገሮችን ይታያሉ፤ እነዚህ አራት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
8. ጳውሎስ እነዚህን እውነቶች ሁሉ መስጠቱ ለምን እንዲያገለግላቸው ነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ ሌሎችን ወገኖችንም ሆነ ራስህን በዚህ እውነት አጽናንተህ ታውቃለህ ወይ? የጌታ መምጣት ለምንገኝባቸው ማናቸውም ከባድ ሁኔታዎች ሁሉ መጽናናት ሊሆነን እንደሚችል ዘወትር ራሳችንን ልናሳስብ ይገባናል፡፡

# ጥናት ስምንት 1ኛ ተሰ 5፡1-11

የጥናት ዓላማ፡- እኛ አማኞች እርስ በእርሳችን የመጽናናት አንዳችን ደግሞ ሌላችንን የማነጽ ነገር አንድ ቀን ወይም ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የምናደርገው ሳይሆን ዘወትር የምንለማመደው ነገር ሲሆን እንደሚገባ ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ስለዚህ በእርግጥ አሁን እንደምታደርጉት ሁሉ እርስ በእርሳችሁ ተጽናኑ፤ አንዱም ሌላውን ያንጽ፡፡›› 1ኛ ተሰ 5፡11

1. 1ኛ ተሰ 5፡1-11 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2 ለምንድነው ጳውሎስ ስለ ዘመናትና ወራት ለተሰሎንቄ አማኞች መጻፍ እንደማያስፈልገው የየሚናገረው? ‹‹እናንተ ራሳችሁ በሚገባ ታውቃላችሁ›› ሲል እነዚህ ሰዎች ይህንን እውቀት ከየት ያገኙት ይመስልሃል? አንተስ ስለ ዘመኑና ስለወቅቱ ምን ያህል እውቀት አለህ?
2. በቁ1-3 ስንመለከት የጌታን ምጽአት ከሁለት ነገሮች ጋራ በማነጻጸር ሲናገር እናያለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እነዚህ ሁለት ነገሮች ከጌታ ምጽአት ጋራ የሚያመሳስላቸው ዋነኛ ነገር ምንድነው?
3. ‹‹ሰዎች›› በማለት በቁ3 ላይ የሚጠቅሳቸው እነማንን ነው ብለህ ታምናለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
4. በቁ4-5 ላይ ‹‹እናንተ ግን›› በማለት የሚናገረው ስለማን ነው? የጌታን መገለይ አማኝ መፍራትና መደንገጥ የማይኖርበት ሐዋርያው የሚናገራቸው ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ የጌታን መገለጥ ስታስብ ፍርሃት ልብህን የሚሞላው ከሆነ ከእርሱ ጋራ ያለህን ግንኙነት መመርመር ያስፈልግሃል፡፡
5. አማኞች የጨለማና የሌሊት ልጆች ሳይሆኑ የብርሃን ልጆች በመሆናቸውን ማድረግ የሚገባቸውና በቁ6-7 የተነገሯቸው ምን ነገሮችን ታያለህ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የአማኞችን ሁኔታ የሚያነጻጽረው ከማን ጋራ ነው? ለምን?
6. የቀን ሰዎች የሆኑት መኖር ስለሚገባቸውና ስለሚጠበቅባቸው አኗኗር ቁ8 ምን ይነግረናል? በነዚህ ነገሮች ራስህን ስትመዝን ራስህን የቀን ሰው ማለትም በብርሃን እንደሚመላለስ ሰው ሆነህ ታየዋለህ ወይ?
7. በቁ7 ላይ የተጠቀሰው እንቅልፍና በቁ10 ላይ የተጠቀሰው እንቅልፍ አንድ ናቸው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን? በቁ10 አነጋገር ክርስቶስ ስለእኛ ስለሞተበት ምክንያት ምን እንማራለን?
8. በቁ11 መሰረት አማኞች ለእርስ በእርሳቸው እንዲያደርጉ የሚያበረታታቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? የተሰሎንቄ አማኞች እነዚህን ሁለት ነገሮች አስመልክቶ ህይወታቸው ምን ይመስላል? የጳውሎስ ማበረታቻ ለእነዚ ሰዎች ምን የሚል ነው? በህይወትህ እነዚህን ሁለት ነገሮች ይታያሉ ወይ? በህይወትህ የማይታዩ ከሆነ ልትኮተኩታቸው፤ በመልካም እየተለማመድካቸውም ካሉ ደግሞ በዚያው እንድትገፋበት እንደሚገባ ጳውሎስ ይነግርሃል፡፡

# ጥናት ዘጠኝ 1ኛ ተሰ 5፡12-28

የጥናት ዓላማ፡- የነገር ሁሉ መመዘኛ ከሆነው ከእግዚአብሄር ቃል በቀር፤ ማናቸውንም ዓይነት ወደ ህይወታችን የሚመጡ ነገሮች በሙሉ ለመቀበልም ሆነ ለመጣል በቃሉ የመመዘንን ልምድን ልናዳብር እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹የመንፈስን እሳት አታዳፍኑ፤ትንቢትን አትናቁ፡፡ ሁሉን ነገር ፈትኑ፤ መልካም የሆነውን ያዙ፤ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ፡፡›› 1ኛ ተሰ 5፡18-22

1. 1ኛ ተሰ 5፡12-28 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ12 ላይ እንድናከብር ጳውሎስ የሚለምነን እነማንን ነው? 1ኛ ጴጥ 5፡3 ጋራ በማስተያየት ‹‹የበላዮቻችሁ›› የሚለው አነጋገር ስለማን ነው ብለህ ታምናለህ?
2. ለምንድነው እነዚህ ሰዎች በፍቅር እጅግ እንዲከበሩ ጳውሎስ የሚያዘው? በትጋት ለሚሰሩ፣ ለበላዮችህና፣ መካሪ ለሆኑህ ሰዎች የዚህ ዓይነት ፍቅርና አክብሮት ትሰጣለህ ወይ? ካልነስ ለምን?
3. በቁ14 ላይ የምናያቸው ሶስት ዓይነት ሰዎች ማን ማን እንደሆኑ ተናገር፡፡ አማኝ እንደ ሶስቱ አይነት ሰዎች ሲገጥሙት ሲገጥሙት መውሰድ ስለሚኖርበት እርምጃ ጳውሎስ የሚያዘው ምንድነው? ለእያንዳንዱ የሚወስደው እርምጃ መለያየቱ ምን ያስተምረናል?
4. ጳውሎስ በቁ15 ላይ አጥብቆ የሚያስጠነቅቀው ነገር ምንድነው? ክርስትያኖች እንዲያደርጉት በዚሁ ቁጥር ላይ የሚያበረታታው ነገርስ ምንድነው? ‹‹ተጣጣሩ›› የሚለው የጳውሎስ አነጋገር ምን ያሳይሃል? በክፉ ፈንታ ክፉ አለመመለስና፤ ለሰዎች መልካም የሆነውን ማድረግ በሚሉት ሚዛኖች የራስህን ህይወት ስትመዝን የት ታገኘዋለህ?
5. የእግዚአብሄርን ፈቃድ አስመልክቶ ከቁ16-18 የምንረዳው እውነት ምንድነው? ይህ በእያንዳንዳችን ህይወት ውስጥ ሲተረጎም ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል አስረዳ፡፡
6. 1ኛ ተሰ 1፡10 2፡19 3፡13 4፡16-18 5፡23 ትን በማንበብ አምስቱንም ምዕራፎች ያዘሉት አንድ ተመሳሳይ እውነት ምን ታያለህ? ቁ23-24 ለጌታ ምጽአት ህይወታችንን ማዘጋጀት አስመልክቶ እግዚአብሄር ስላለው ሃላፊነት ምን ታያለህ?
7. ቁ19-22ትን መለስ ብለን ስናይ የታዘዝናቸውን አምስት ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡ ሐዋ ሥራ 17፡11 የምናያቸው ሰዎች ከነዚህ ውስጥ የትኛውን መመሪያ ሲጠቀሙ ነው የምናየው? ለመፈተን የተጠቀሙበትስ ነገር ምን ነበረ? አንተስ እንደነሱ የማድረግ ልምድ አዳብረሃል ወይ? የማናቸውም ነገር መመዘኛ ተደርጎ የተሰጠን የእግዚአብሄር ቃል ስለሆነ ቃሉ ለሁሉ ነገር ሚዛን ሊሆንህ ይገባል፡፡